29 **725/2013**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Urban Development & Construction

ተ/1-810/2/209/1
29/1/2006

ለከተሞች መልካም አስተዳደርና አቅም ግንባታ ቢሮ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

ጉዳዩ፡- የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ፤

የ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት የልማት ኃይሎች እውቅና መስጫ መመሪያ ቁጥር 29/2005 ሆኖ ከጳጉሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም. ጀምሮ የፀደቀ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በዚሁ መሠረት መመሪያውን እንድታስፈጽሙ የፀደቀው መመሪያ 1 ጥራዝ ሰነድ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ የተላከ መሆኑን እየገለጽን የሰነዱ ግልባጭ የተመዘገበላችሁም እንድትከታተሉት እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ማርያም
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (ከተማ ልማት ዘርፍ)
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ (ኮንስትራክሽን ዘርፍ)
- ለህብት ሥራ አመራርና ማስተባበሪያ ቢሮ
- ለህግ አገልግሎት መመሪያ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት አብይ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት ቴክኒክ ኮሚቴ
- ለ5ኛው የከተሞች ሳምንት የፓናል ውይይት ዝግጅት ኮሚቴ

ከ/ል/ኮ/ሚ/ር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት
ETHIOPIAN CITIES WEEK

ባህር ዳር
Bahir Dar

# የልማት ኃይሎች እውቅና መስጫ
# መመሪያ ቁጥር 29/2005

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የሀገራችንን ራዕይ እውን ከማድረግ አንፃር የሚጫወተው ሚና ጉልህ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን በተለይም ደግሞ አሁን በያዝነው የልማት ምዕራፍ ከተሞችን የኢንዱስትሪ መዳረሻ እንዲሆኑ ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ ተልዕኮ ተሰጥቶታል። የተልዕኮ ስኬቱ የልማት ኃይሎችን የጋራ እንቅስቃሴና ርብርብ የሚጠይቅ ሲሆን ከሁሉ በላይ ደግሞ የሰፊው የከተማ ነዋሪ ንቅናቄ ስምረት እንደሆነ እሙን ነው። ይህንን ንቅናቄ ለመፍጠርና ተልዕኮውን ለማሳካት በርካታ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ያሉ ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንዱ በየዓመቱ የሚከበረው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ነው።

በዚሁ መሰረት በየዓመቱ በሚከበረው የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ላይ ከሚከናወኑት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ ሚኒስትሩ ለሚመራቸው ዘርፎች እድገት ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የልማት ኃይሎች እውቅና መስጠት ነው። ከዚህ አንፃር የልማት ኃይሎች አስተዋፅኦ በየደረጃው በመለየትና በመገምገም ምርጥ ተሞክሮን ለመቀመርና ለማስፋት ብሎም በርካታ ሞዴሎች እንዲወጡ ለማጠናከር የሚያስችል ግልፅና ፍትሃዊ የአሰራር ስርዓት መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

በመሆኑም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ዘርፉን ከመምራት አንፃር በተሠጠው ስልጣን መሰረት ይህን የልማት ኃይሎች እውቅና መስጫ መመሪያ አውጥቷል።



## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ የልማት ኃይሎች እውቅና መስጫ መመሪያ ቁጥር 29/2005 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚየሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) ***"የልማት ኃይሎች"*** ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፎች ተልዕኮን በማሳካት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ያበረከቱ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ የሥራ ተቋራጮች፣ አማካሪዎች፣ የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት፣ የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምክር ቤት አባል ተቋማት እና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተባባሪ ድርጅቶች ናቸው፣

2) ***"የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት "*** ማለት *የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ* እና *የአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ* የሚያከትት ሲሆን እነዚህም፡- *የጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ* የኢንተርኘራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች የሚያሠማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50000 ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100000 ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ፣ *የአነስተኛ ኢንተርፕራይዝ* የኢንተርኘራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሠራተኞችን ጨምሮ ከስድስት እስከ ሰላሣ ሰዎች ቀጥሮ የሚያሰማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50001 እስከ 500000 ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100001 እስከ 1500000 ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ማለት ነው፣

3) **የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ስልጥና ተቋማት** ማለት የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ስልጠና የሚሰጡ የትምህርት ተቋማት ናቸው፡፡

4) **የሥራ ተቋራጮች (ኮንትራክተሮች)** ማለት በግንባታ ስራ ላይ የተሰማሩና የተለያዩ ደረጃዎች ያሏቸውን የግንባታ የስራ ተቋራጮች ማለት ነው፡፡

5) **አማካሪዎች (ኮንሰልታንቶች)** ማለት በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዙሪያ በማማከር አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አማካሪዎች ማለት ነው፡፡

አዲስ አበባ

6. የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ምክር ቤት አባላት ተቋማት ማለት ተልዕኮዋቸውን ሲያስፈጽሙ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በማደራጀት፣ ድጋፍ በመስጠትና ስራ ላይ በማስማራት በርካታ የስራ ዕድል እንዲፈጠሩ ለማስቻል በፌደራል ደረጃ የተቋቋመው ምክር ቤት አባል ተቋማትን ያካትታል፣

7. አነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ማለት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ከማብቃት አንጻር በከተሞች የአንድ መስኮት አገልግሎት የሚሰጡትን ማለት ነው፣

8. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተባባሪ ድርጅቶች ማለት በከተማ ልማትና በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለከተሞች ልማትና ዕድገት የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኙ ድርጅቶችን ማለት ነው፣

9. «ሚኒስቴር» ማለት የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ማለት ነው፣

10. «ክልሎች» ማለት በኢትዮጵያ ፌ/ዲ/ሪ/ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ሥር የተመለከቱ ዘጠኙን ክልሎች ሲሆን ለመመሪያው አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና ድሬዳዋ አስተዳደሮችን ያጠቃለለ ነው።

## 3. ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. ለከተሞች እድገት መፋጠን እና መልካም አስተዳደር መስፈን ጉልህ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የልማት ኃይሎች እዉቅና በመስጠት ለበለጠ ስራ እንዲነሳሱ ለማስቻል፣

2. መልካም ተሞክሮዎቻቸውን በመለየት፣ በመቀመር እና ለሌሎች እንዲስፋፉ ለማድረግ ነው።

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ ተፈጻሚ የሚሆነው በ2006 ኣ.ም ለሚከበረው 5ኛው የከተሞች ሳምንት ሆኖ እውቅና የሚሰጥበት በ2005 ዓ.ም የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ተልዕኮን በማሳካት ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ባበረከቱ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትእና የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ዘርፍ ተባባሪ ድርጅቶች ላይ ይሆናል።

# ክፍል ሁለት

## የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች መምረጫ መስፈርት

የዚህ መስፈርትና እና የአፈፃፀም መመሪያ ዋነኛ ዓላማ ሞዴል ከሆኑ ኢንተርፕራይዞች የተገኙ የምርትና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለሌሎች ኢንተርፕራይዞችና ለህብረተሰቡ በማስተዋወቅ ትምህርት እንዲቀሰምበት ሲሆን ቼክሊስቱም በሁሉም ከተሞች የሚገኙ ሞዴል እና ታዳጊ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን መልምሎ ለማቅረብና በኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት ዝግጅትም ውጤታማ የሆኑ ምርጥ ኢንተርፕራይዞችን ለመሸለም የሚያስችል ይሆናል

5. የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መርሆዎች

1) መስፈርቱና እና የአፈፃፀም መመሪያው በየደረጃው በሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ታይቶ ይሁንታ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

2) በየደረጃው የሚገኙ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች ስለ መስፈርቱና እና የአፈፃፀም መመሪያው አጠቃቀም ግንዛቤ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3) ነባርና ሞዴል ኢንተርፕራይዞች በቅፅ እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡

4) መዝጋቢውም አካል መረጃው ትክክለኛ መሆኑን ያረጋግጣል የሚመለከተው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ ያፀድቃል፡፡ በቅጹ ክብ ማህተም ያርፍበታል፡፡

5) በየደረጃው ምርጫውን የሚያከናውን ኮሚቴ ይዋቀራል፤

6) በመስፈርትና እና በአፈፃፀም መመሪያ መሠረት እያንዳንዱ ክልል በየደረጃ ተመርጠው ከቀረቡለት ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ኮንስትራክሽን፣ ከእንጨት ከብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣ የምግብ ዝግጅት፣ ከከተማ ግብርና እና ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት የሥራ ዘርፎች ከእያንዳንዱ የሥራ መስክ አንድ አንድ ምርጥ ኢንተርፕራይዞችን እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

7) ስለመመረጣቸውም በቅጹ ላይ የሚመለከታቸው የኮሚቴ አባላት ይፈራረማሉ፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ክብ ማህተምም ያርፍበታል፡

8) የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ልማት ኤጀንሲ በመስፈርትና እና በአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ከክልሎች ተመርጠው ከቀረቡለት ተቋማት ውስጥ ከየዘርፉ ከአንድ እስከ ሦስት የወጡትን በመለየት ለሽልማት ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይልካል፣

6. ቅድመ - ሁኔታዎች

1) የኢንተርፕራይዙ የንግድ ፍቃዱ/የማህበር ምስክር ወረቀቱ የታደሰና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው፣

2) ለኢንተርፕራይዙ ቅጥር ሰራተኞችና ለአባላት ክፍያ የተደረገበት የክፍያ ሰነድ፣

3) የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተሟላ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ፣

4) በመስፈርቱ የቀረቡ ነጥቦች ላይ የሚያወዳድራቸው ጉዳዮችን በኤግዚቢትነት ይዞ መገኘት /በፎቶ ወይንም በቪዲዮ ይዞ መቅረብ / የሚችል፣

5) በሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫና ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት ማንዋል መሥፈርት ተገምግሞ ለውድድር ከ75% በላይ ውጤት ማግኘት አለበት፡፡

7. የተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞች የስራ መስክና መመልመያ መስፈርቶች፤

1) በ2006 ዓ.ም. 5ኛው ዙር የኢትዮጵያ የከተሞች ሳምንት በዓል ላይ ለመሳተፍ የሚመረጡትሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሁሉም ከዕድገት ተኮር ዘርፎች የማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽን፣ ከተማ ግብርናና አግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ማዘጋጃቤታዊ

አገልግሎቶች፣ ማዕድንና ኬሚካል ምርት ስራዎች እንዲሁም ከፌጠራና የቴክኖሎጅ ስራዎች ይሆናሉ፣

2) በዝርዝር ሲታይ ከጨርቃ ጨርቅና አልባሳት፣ ከቆዳና ቆዳ ውጤቶች፣ ከእንጨት፣ ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ፣ ከኮንስትራክሽን፣ ከአግሮ-ፕሮሰሲንግና የከተማ ግብርና ዘርፎች፣ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች፣ ማዕድንና ኬሚካል ምርት ስራዎች እንዲሁም በቴክኖሎጅና የፈጠራ ስራዎች ላይ የተሰማሩ ሲሆን እንደ ሥራ ባህርያቸው የጋራና የተናጠል የመምረጫ መስፈርቶችን ለመጠቀም ታሳቢ ይደረጋል፣

3) እንዲህም ቢሆን ከኮንስትራክሽን ዘርፎች የሚመረጡት ቋሚ ስራዎች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። በዚህም መሰረት ከሞጁል መምረጫ መስፈርቶች በተጨማሪየሚከተሉትን ዋና ዋና ነጥቦች በማወዳደሪያነት ግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ ይገባል።

## 8. በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ዘርፍ (በሽመና ውጤቶች፣ በሹራብ ስራ፣ በልብስ ስፌትና በጥልፍ ስራ) ለተሰማሩ ኢንተርፐራይዞች፤

1) ለሚያመርታቸው ምርቶች የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን የሚጠቀም መሆኑ፣
2) የሚያመርታቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣
3) ከተገልጋይ እይታ አንጻር የምርቶቹ ዲዛይንና ማራኪነት፣
4) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣
5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣
6) ለውጭ ሀገር ገበያ ሊቀርብ የሚችል ጥራት ያለው ምርት እያቀረበ የሚገኝ/ማቅረብ የሚችል መሆኑ የሚሉት ናቸው።

## 9. በቆዳናቆዳውጤቶችሥራየተሰማሩ፤

1) ለሚያመርታቸው ምርቶች የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃን የሚጠቀም መሆኑ፣
2) የሚያመርታቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣
3) ከተገልጋይ እይታ አንጻር የምርቶቹ ዲዛይንና ማራኪነት፣
4) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣
5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣
6) ለውጭ ሀገር ገበያ ሊቀርብ የሚችል ጥራት ያለው ምርት እያቀረበ የሚገኝ/ማቅረብ ሚችል መሆኑ የሚሉት ናቸው።
7) በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ/ለማስወገድ ያደረገው ጥረት በዋነኝነት ታሳቢ፣ የሚደረጉ ጉዳዮች ናቸው።

10. የእንጨት፣ብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ መስክ የተሰማሩ፣

በዚህ ዘርፍ የሚጠቃለሉት ዋና ዋና የስራ መስኮች የእንጨትና የቀርቀሃ ውጤቶችና የብረታብረትናኢንጂነሪንግ ናቸው፡፡

1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሳሪያ መጠቀማቸው፣

2) የሚያመርታቸው ምርቶች ከውጭ የሚገቡትን የሚተኩ መሆናቸው፣

3) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

4) መ/በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ ስለመሆናቸው፣

5) የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

11. **በኮንስትራክሽን የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ፤**

በዚህ ዘርፍ የሚጠቃለሉት በግንባታ ግብዓት አቅራቢነት (ፐሪኬስት፣ ብሎኬት፣ጥርብ የኮብል ስቶን ማቅረብ፣ አግሮ ስቶን፣ ጅብሰም ቦርድ፣ ጠጠር፣) እና የግንባታ አገልግሎት ስራዎች፣ የግንባታ ስራ፣ የማጠናቀቂያ ስራዎች፣የመንገድ ስራ፣የኤሌክትሪክ ዝርጋታ፣ የቧንቧ ስራ እና የሳኒቴሽን ስራዎች የተሰማሩትን የሚያጠቃልል ሆኖ፣

1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው፣

2) የሚፈለገውን ያህል ምርት በብዛት ለማምረት የሚያስችል የተለየ አሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣

3) በኢንተርፕራይዙ ውስጥ የሚገኙ ባለሙያዎች የሙያ ብቃት ምዘና ያለፉ መሆናቸው፣

የጠባቂነትና የጥገኝነት አመለካከትና ዝንባሌ የሌለው መሆኑ፣

4) ለኮንስትራክሽን አገልግሎት የሚውል ለየት ያለ የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ጥቅም ላይ ማዋሉ፣

5) በኮንስትራክሽን ሥራ ላይ የመልካም ሥራ ማረጋገጫ ያለው መሆኑ በዋነኛነት የሚዳሰሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

12. **የከተማ ግብርና፤**

በዚህ ዘርፍየሚጠቃለሉት በከተማ እርሻ ማለትም በአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የእህል ምርት፣ ችግኝና የመሳሰሉት እና በእንስሳት እርባታና ማድለብ ንዑስ ዘርፍበግ፣ ፍየል፣ ዶሮ፣ ንብ፣ ከብት፣ አሳማ በመሳሰሉት የሥራ መስኮች የተሰማሩ ሲሆኑ እነዚህም ፤

1) የሚጠቀምበት የመሬት ይዞታ ስፋት/በአነስተኛ ቦታ ብዙ ማምረት መቻል/፣

2) እንደ ምርቱ ዓይነት /በቀን፣ በሳምንት፣ በወር/ ለገበያ የሚያቀርበው የምርት መጠን፣

3) ዘመናዊ መንገድ የማቀነባበር ወይም የምርቱን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም ያደረገው ጥረት በዝርዝር ሊታዩ የሚገባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

13. አግሮ-ፕሮሰሲንግ እና ምግብ ማቀነባበር የማወዳደሪያ መስፈረቶች የሚከተሉተን ያጠቃልላል፤

1) የኢንተርፕራይዙ ምርት የቆይታ ጊዜና ጣዕም ያለመቀየር ባህርይ፣
2) ከውጭ የሚገቡ የደረቁ ምግቦችን ለመተካት ያደረገው ጥረትና ያስመዘገበው ውጤት፣
3) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛትን ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ፣
4) ምርቶቹ ለውጭ ሀገር ገበያ ቀርበው ተፈላጊ መሆናቸው/ሊያቀርቡ የሚችሉ መሆናቸው፣
5) በአመራረት ሂደቱ የአካባቢን ብክለት ለመቀነስ/ለማስወገድ ያደረገው ጥረትና በተለይም ምርቶቹ ለጤንነት የማያስጉ በመሆናቸው በዋነኝነት ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች የምርት አስተሻሸግ ናቸው፡፡

14. ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች፤

በከተሞች ጎልቶ የሚታየውን የድህነትና ሥራ አጥነት ችግር ለመቀነስ አዋጭ ተብለው ከተለዩትና ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው የሥራ ዘርፎች መካከል የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ሥራዎች ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህ ንዑስ ዘርፍ የሚካተቱት የሥራ መስኮች ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ፣ ቀልገ ማቅለዝ፣ የአካባቢ /መንገድ/ ጽዳት፣ የሕዝብ ንጽህና ቤቶች አገልግሎት፣ የከተማ ማስዋብ ሥራ እና የዘላቂ ማረፊያ ቤት ማዘጋጀትና አካባቢውን ማስዋብ ሥራዎች ይገኙበታል፡፡
በዚህ የሥራ ዘርፍ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ እንደሌሎች ኢንተርፕራይዞች ለመወዳደር ከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሊታዩ ይገባል፡፡

1) ደረጃውን በጠበቀ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ደረቅ ቆሻሻዎችን የማስወገድ ሁኔታ፣
2) የተሰበሰቡ ቆሻሻዎችን በመልሶ ዑደት በመጠቀም ለአገልግሎት የማዋል ደረጃ፣
3) ኢንተርፕራይዙ በከተማው ውስጥ ያስዋባቸው አካባቢዎች ብዛት፣

15. ማዕድንና ኬሚካል ስራዎች፤

በማዕድን የስራ መስክ እና በኬሚካል የስራ ዘርፍ ለሚወዳደሩ ኢንተርፕራይዞችከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሊታዩ ይገባል፡፡

1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው፣
2) ከውጭ ሀገር የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት መቻላቸዉ፣

የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

3) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛትን ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆን፣

## 16. የዕደ-ጥበብ ውጤቶች፤

በዚህ የስራ ዘርፍ ለሚወዳደሩ ኢንተርፕራይዞችከሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫ መስፈርት በተጨማሪ የሚከተሉት ነጥቦች ሊታዩ ይገባል፡፡

1) በራሳቸው ወይም በሌላ ኢንተርፕራይዝ በአገር ውስጥ በተሰራ የማምረቻና መገልገያ መሣሪያ መጠቀማቸው
2) ኢንተርፕራይዙ የምርት ጥራትና ብዛት ለማሻሻል የተለየ የአሰራር ዘዴ ያለው መሆኑ
3) የአካባቢ ባህላዊ እሴቶችን የሚያንጸባርቅ
4) ከፍተኛ የቱሪስት መስህብነት ደረጃ ያላቸው
5) በማንኛውም ዘርፍ የተለየ የፈጠራ ስራ ያላቸው ጥቃቅንና አነስተኛ ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ተወዳድረው ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡

## 17. በውድድሩ የሚካተቱት ኢንተርፕራይዞች፤

በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ መስፈርቱን አሟልተው በሞዴልነት የተመለመሉና በ4ኛውና ከዚያበፊት በተካሄዱ ሀገር አቀፍ የከተሞች ሳምንት በዓላት ላይ ያልተሸለሙ እና አዳዲስ ሞዴሎች መሆን ይሆናሉ፡፡

## 18. ለኤግዚቢሽን የሚቀርቡ ምርቶች፤

1) ተሳታፊ ኢንተርፕራይዞች በበዓሉ ወቅት ናሙና ምርቶቻቸውን ለኤግዚቢሽን ያቀርባሉ፡፡
2) የሚቀርቡ ምርቶችና ቴክኖሎጂዎች ደረጃቸውን የጠበቁና በራሳቸው በአቅራቢ ኢንተርፕራይዞች የተመረቱ ብቻ ስለመሆናቸው ለኤግዚቢሽን ከመቅረባቸው በፊትም ሆነ በበዓሉ ወቅት ተገቢው ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡
3) የምርቶችን ጥራት፣ የተጠቃሚዎችን እርካታና የኤግዚቢሽን አቀራረቡን መነሻ በማድረግ ውጤት ይሰጣል፡፡
4) የምርት ናሙና ለማቅረብ የማይችሉ ኢንተርፕራይዞች ለምሳሌ፣ በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሆኑና በቀላሉ ለማጓጓዝ የማይመቹ ዕቃዎችን የሚያመርቱ ከሆነ በስዕላዊ መግለጫና በቪዲዮ ማሳያዎች ማቅረብ ይችላሉ፡፡
5) ሆኖም ግን የቀረበውን ስዕላዊ መግለጫና ቪዲዮ ምርቶቹ/አገልግሎቶቹ የራሳቸው ለመሆኑ በክልል /ከተሞች/ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ /ቢሮ/ በማሕተም መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

19. የቅድመ ማወዳደሪያ መስፈርቶችና መቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች፣

1) የኢንተርፕራይዙ የንግድ ፍቃዱ/የማህበር ምሥክር ወረቀቱ የታደሰና የግብር ከፋይነት መለያ ቁጥር ያለው፣

2) ለኢንተርፕራይዙ ቅጥር ሰራተኞችና ለአባላት ክፍያ የተደረገበት የክፍያ ሰነድ፣

3) የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት ወይም የተሟላ የሂሳብ መዝገብና ሰነድ፣

4) በመስፈርቱ የቀረቡ ነጥቦች ላይ የሚያወዳድራቸው ጉዳዮችን በኤግዚቢትነት ይዞ መገኘት /በፎቶ ወይንም በቪዲዮ ይዞ መቅረብ /የሚችል፣

5) በሞዴል ኢንተርፕራይዞች መምረጫና ምርጥ ተሞክሮ የማስፋት ማንዋል መስፈርት ተገምግሞ ለውድድር ከ75% በላይ ውጤት ማግኘት፣

6) ከሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መካከል በከተሞች ሳምንትመሳተፍ የሚችሉት በዚህ መመሪያ በተቀመጡት መስፈርቶች ተመዝነው አጠቃላይ አፈጻጸማቸው 75% እና ከዚያ በላይ ያላቸው ሲሆኑ ነገር ግን የኢንተርፕራይዙ ባለቤቶች ወይም/አባላት 50%እና ከዚያ በላይ የሚሆኑት ሴቶች ከሆኑ መመዘኛ ነጥቡ 70% እና ከዚያ በላይ ይሆናል፡፡

20. የማወዳደሪያ መስፈርቶች አተገባበር፣

1) በዘርፉ ያለው የቆይታ ጊዜ፣

ሀ. እስከ 1 ዓመት ---------------------- 10 ነጥብ

ለ. ከ1-2 ዓመት ------------------------ 9 ነጥብ

ሐ. ከ2-3 ዓመት --------------------------8 ነጥብ

መ. ከ3-4 ዓመት --------------------------7 ነጥብ

ሠ. 5 ዓመት -------------------------------6 ነጥብ

ረ. ከ5 ዓመት በላይ ----------------------2 ነጥብ

2) የካፒታል ዕድገት ልዩነትን በተመለከተ፣

ሀ. ከመነሻ ካፒታሉ ሁለት እጥፍ በላይ ያስመዘገበ ---------- 20 ነጥብ

ለ. የመነሻ ካፒታሉን አንድ እጥፍ ያስመዘገበ --------------- 16 ነጥብ

ሐ. የመነሻ ካፒታሉን ከ75%-----99%----------------------- 14 ነጥብ

መ. የመነሻ ካፒታሉን ከ50%- ---74%- -------------------- 12 ነጥብ

ሠ. የመነሻ ካፒታሉን 25%- ---- 49%- ------------------- 10 ነጥብ

ረ. የመነሻ ካፒታሉን ከ10%- --- 24%- ------------------- 8 ነጥብ



አዲስ አበባ

ሰ. የመነሻ ካፒታሉን ከ1%- ---- 9%- ---------------------- 6 ነጥብ

ሸ. የመነሻ ካፒታሉን እስከ 1%- --------------------------------- 2 ነጥብ

3) የተለየ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

ሀ. በኢንተርፕራይዙ በራሱ ተቀድቶ የተባዛና ሥራ ላይ የዋለ ከሆነ ---- 1ነጥብ፣

ለ. በሀገር ውስጥ በሌሎች ኢንተርፕራይዞች የተቀዳና የተባዛ ከሆነ ---- 10 ነጥብ፣

ሐ. ከውጭ ሀገር ገብቶ ያለምንም ማሻሻያ ሥራ ላይ የዋለ ከሆነ ------------8 ነጥብ፣

4) ለሌሎች የፈጠረውን የስራ ዕድል በተመለከተ፤

ሀ. ከ30 ሰው በላይ -------------15 ነጥብ

ለ. ከ25 — 29 ሰው------------ 14 ነጥብ

ሐ. ከ20 --- 24 ሰው ---------- 13 ነጥብ

መ. ከ15 — 19 ሰው ---------- 10 ነጥብ

ሠ. ከ10 --- 14 ሰው ---------- 6 ነጥብ

ረ. ከ5 --- ---9 ሰው ------------ 4 ነጥብ

ሰ. ከ1--- ----4 ሰው ---------------2 ነጥብ

5/ ምርታማነትን በተመለከተ፤

ሀ. ምርት ለማምረት/አገልግሎት ለመስጠት ከሌሎች ተመሳሳይ ኢንተርፕራይዞች የተለየ ፈጣን የአሰራር ዘዴ እና ብዛት ያለው ምርት ማምረት ---------- 5

ለ. በኢንተርፕራይዙ ውስጥ ያሉ አንቀሳቃሾች ከሌሎች ኢንተርፕራይዞች አንጻር በተመሳሳይ ጊዜ፣ በተመሳሳይ የማምረቻ መሣሪያና ጥሬ ዕቃ መጠን በፍጥነትና በብዛት ማምረት መቻላቸው ---5

6) የምርት ጥራት፤

የምርቱ/አገልግሎት ጥራቱ በተነጻጻሪ ከሌሎች የተሻለ መሆኑ በደንበኞች የተረጋገጠ -- 10

7) ኢንተርፕራይዙ በሞዴልነት ሲመረጥ ያገኘው ነጥብ፤ .

ሀ. ከ90% በላይ----------20

ለ. ከ85-90%------------18

ሐ. ከ80-84%------------16

መ. ከ75-79%------------14

ሠ. ከ70-74%------------10

725/2013

21. የምልመላ አፈጻጸምና የውጤት አገላለፅ ሂደቶች፤

1) በየደረጃው ለሚደረገው የምርጫ ሂደት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣ ከአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋም፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ የወጣቶችና የሴቶች ፎረም ተወካዮች ያካተተና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ተወካይ ሰብሳቢ የሆነበት ኮሚቴ ይዋቀራል።

2) በየከተማው/ክፍለ ከተማው/ወረዳው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤቶች ከነባር የኢንተርፕራይዞች መዝገብ በመነሳት በተገቢው ያማወዳደሪያ መስፈርት ከእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ አኳያ ነጥብ በመስጠትና ውጤት ላይ በመድረስ ከአንደኛእስከ 4ኛ የወጡትን ለምርጫ ከአቀረቧቸው አጪዎች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለዞን የጥ/አ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3). እያንዳንዱ የዞን ጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤቶች/መምሪያዎች ከየወረዳዎች ከየሥራ መስኩ ተመርጠው የተላኩትን ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በማጣራት ከቀረቡለት ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ከየሥራ መስኩ በማወዳደሪያ መስፈርቱ አወዳድሮ ከየመስኩ ከ1ኛ እስከ 4ኛ የወጡትን ለምርጫ ከአቀረቧቸው ዕጩዎች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ መረጃውን ይልካል፡፡

4) እያንዳንዱ የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየዞኑ/ከተሞች ተመርጠው የተላኩለትን ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሠረት በማወዳደር በክልል ደረጃ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ደረጃ ያገኙትን ሞዴሎች ከየሥራ መስኩ በመለየት በሚመለከተው የክልል የበላይ አካል በማጸደቅ በዕጩነት ካወዳደራቸው ኢንተርፕራይዞች ሙሉ ዝርዝር መረጃ ጋር ለፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፡፡

5) የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርን በተመለከተ፡-

ሀ) የወረዳየጥቃቅንናአነስተኛኢንተርፕራይዞችልማትጽ/ቤትለክ/ከተማውየጥ/አ/ኢ/ልጽ/ቤት፣

ለ) የክፍለ ከተማው የጥ/አ/ኢ/ል ጽ/ቤት ለከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢን/ል/ኤጀንሲ፣

ሐ) የከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ከየሥራ መስኩ አንደኛ የወጡትን በሚመለከተው የበላይ አካል በማጸደቅ ለፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል።

6) የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርና የሀረሪ ክልልን በተመለከተ፤

ሀ) የቀበሌ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለከተማው ጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲ

ለ) የከተማው/የክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ በሚመለከተው የበላይ አካል በማጸደቅ ለፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፡፡

6) የፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየክልሉ ተመርጠው የተላኩለትን ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃ አጣርቶ ከከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ጋር በመመካከር ኢንተርፕራይዞቹ በ5ኛው የኢትዮጵያ ከተሞች ቀን ምርቶቻቸውን ለኤግዚቢሽን ማቅረብ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

7) በከተሞች ቀን ተሳታፊ የሆኑት ሁሉም ኢንተርፕራይዞች የዕውቅናና ተሳትፎ ሽልማት የሚሰጣቸው ሲሆን ከመካከላቸው ቀደም ሲል ባስመዘገቡት ነጥብ መነሻነትና በኤግዚቢሽን አቀራረባቸውና የደንበኞችን እርካታ መሰረት በማድረግ በሚሰጠው ነጥብ

ተመዝነውከአጠቃላይ ተሳታፊዎች መካከል ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ የወጡት በፌደራል ደረጃ አሸናፊ ሆነው ልዩሽልማት እንዲሸለሙ ይደረጋል፡፡

8) አጠቃላይ የምልመላ ስራው የሚከናወነው በተመሳሳይ መንገድ ሆኖ ነገር ግን ልዩ ድጋፍ የሚሹና በተሻለ ደረጃ ላይ ያሉት ክልሎች ሰየብቻ የሚወዳደሩበት ዕድል በፌደራል ደረጃ ይመቻቻል፡፡

22. **በፌደራል ደረጃ የሚሸለሙ 3(ሶስት) ኢንተርፕራይዞች ማወዳደሪያ መስፈርቶች፤**

1) የሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣የኦዲት ሪፖርትና አጠቃላይ የመረጃ አያያዝ፣
2) የሀብትና እዳ መግለጫና ያስመዘገበውየካፒታል መጠን፣
3) ለሌሎች የተፈጠረ የስራ እድል፤
4) የቴክኖሎጅ አጠቃቀሙ፤
5) አዳዲስ የፈጠራ ስራዎች እና ኢንተርፕራይዙን ለማስፋፋት የተደረጉ ጥረቶች፤
6) አመታዊ ሽያጭና ትርፍ፤
7) የኢንተርፕራይዙ ባለቤት/አባላት ወረሃዊ ክፍያና በግል ህይወታቸው ያሳዩት ለውጥ፤
8) የኢንተርፕራይዙ የቁጠባ መጠን፤

23. **የተሳታፊዎች መጠን/ኮታ በዘርፍ፤**

1) እንደ አጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃና ከእያንዳንዱ ክልል ተመልምለው በ5ኛው ዙር የኢትዮጵያ ከተሞች ሳምንት በዓል ላይ ከሚሳተፉት ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጠቅላላ መጠን ውስጥ ከ90% በላይ የሚሆኑት በዕድገት ተኮር/ማኑፋክቸሪንግ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ መሆን አለባቸው፤
2) ከማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች የሚመረጡት ኢንተርፕራይዞች ብዛት በማንኛውም ሁኔታ ከ10% መብለጥ የለበትም፡፡

24. **የተሳታፊ ኢንተርፕራይዞች የወጪ አሸፋፈን፤**

1) በዓል ላይ የሚሳተፉት ሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በሚኖሩበት ከተማ ስር ተጠቃለው በበዓሉ ላይ ይሳተፋሉ፤
2) የኤግዚቢሽን ማሳያ ቦታውም ከከተሞቻቸው ጋር አንድ ላይ ይሆናል፤
3) ለኢንተርፕራይዞቹ የሚያስፈልግ የመጓጓዣያና የተሳትፎ አጠቃላይ ወጪ በከተሞች /በክልሉ/ ይሸፈናል፡፡

25. **የመስፈርቶች እና የአፈፃፀም መመሪያው የመተግበሪያ ስልቶች፤**

1) መስፈርቱና እና የአፈፃፀም መመሪያው ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት በየደረጃው በሚገኙ አመራሮችና ባለሙያዎች ዘንድ ይሁንታ እንዲያገኝና ግልጽነት እንዲፈጠር ይደረጋል፤

2 ከምርጫው በፊት ሁሉም ነባርና አዲስ ሞዴል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት እንዲመዘገቡና መረጃውም ከከተማ//ክፍለ ከተማ/ወረዳ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤቶች ጀምሮ እየተረጋገጠና በእያንዳንዱ ቅጽ ላይ ማህተምና ኮሚቴዎች ፊርማ እያረፈበት ደረጃውን ጠብቆ ለክልሎች ይላካል፤

3) ከከተማ ጀምሮ በየደረጃው እስከ ክልል ድረስ ምርጫውን የሚያከናውንና የሚያስፈጽም ኮሚቴ ይዋቀራል፤

2) እያንዳንዱ ክልልና የከተማ አስተዳደር በተቀመጡት የመመዘኛ መስፈርቶች መሰረት በየደረጃው ከየዘርፉ ተመልምለው የተላኩለትን ሞዴሎች ባቋቋመው ኮሚቴ ዓማኒይነት ከአጣራና ካረጋገጠ በኋላ በኤጀንሲው ዳይሬክተር ፊርማ ለፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፣

3) ከየክልሱ ተመልምው የተላኩት ሞዴሎች ዝርዝር በፌደራል ደረጃ በተቋቋመው ኮሚቴ ዓማኒይነት ከተረጋገጠ በኋላ በኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር ፊርማ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እንዲላክ ይደረጋል።

725/2013

## 26. የቴክኒክና ሙያ ተቋማት መምረጫ መስፈርት

ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሴክተር ተልዕኮ መሳካት የበኩሉን ሚና ለተጫወቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማት እውቅና ለመስጠት እንዲቻል ቀጥሎ የተዘረዘሩትን እንደ መምረጫ መስፈርት መጠቀም ይገባል፡-

1) በ2004 ዓ.ም እስከ ሰኔ ወር ስልጠና ያጠናቀቁ ሠልጣኞችን 80% እና ከዚያ በላይ ለሙያ ብቃት ምዘና አቅርበው ከቀረቡትም ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር ብቁ ማድረግ የቻለና ከተለያዩ ቀጣሪ መስሪያ ቤቶች ጋር በመነጋገር ብዙ ሰልጣኞችን ከስራ ጋር ማስተሳሰር ለቻለ 40 ነጥብ፣

2) ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የተቀናጀ ድጋፍ (አራቱንም(የምርታማነት ማሻሻያ፣ የቴክኖሎጂ ድጋፍ፣ የክህሎት ስልጠና፣ የኢንተርፕሩኒየርሺፕ ስልጠና) ወይም በተወሰኑት) በመስጠት የተሻለ ሀብት ማፍራት ያስቻለ 30 ነጥብ፣

3) የአካባቢውን ስራ አጥ ወጣት በአጫጭር ስልጠና በማሰልጠን የስራ ዕድል በስፋት እንዲፈጠር ያደረገ፣ ለአብዛኛው ወጣት የስራ ዕድል የፈጠረ የአካባቢውን ስራ አጥ ወጣት በአጫጭር ስልጠና በማሰልጠን የስራ ዕድል በስፋት እንዲፈጠር ያደረገ 30 ነጥብ የሚሰጠው ሆኖ ጠቅላላ ድምሩ 100 ይሆናል።



## ክፍል ሦስት

## ሞዴል የልማት ኃሎች አመራረጥ ሂደት

27. የጥቃቅናና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች

ከላይ በተገለፀው የማወዳደሪያ መሥፈርት አማካኝነት፡-

ሀ. በየደረጃው ለሚደረገው የምርጫ ሂደት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣ ከአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋም፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ከወጣቶችና የሴቶች ፎረም ተወካዮችን ያካተተና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ተወካይ ሰብሳቢ የሆነበት ኮሚቴ ይዋቀራል፡፡

ለ. በየወረዳው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤቶች ከነባር የኢንተርፕራይዞች መዝገብ በመነሳት በተገቢው የማወዳደሪያ መስፈርት ከእያንዳንዱ ዋናዋና እና ንዑስ የሥራ ዘርፍ አኳያ ነጥብ በመስጠትና ውጤት ላይ በመድረስ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ የተመረጡትን ለምርጫ ከአቀረቧቸው እጩዎች ዝርዝር መረጃ ጋር ለዞን የጥ/አ/ኢ/ል/ጽ/ቤት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐ. እያንዳንዱ ዞን ጥ/አ/ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤቶች ከየወረዳዎች ከእያንዳንዱ ዋናዋና እና ከንዑስ የሥራ መስኩ ተመርጠው የተላኩትን ሁለት ሁለት ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ በማጣራት ከቀረቡለት ኢንተርፕራይዞች ውስጥ ከእያንዳንዱ ዋናዋና እና ከንዑስ የሥራ መስኩ በማወዳደሪያ መስፈርቱ አወዳድሮ ከየመስኩ አንደኛና ሁለተኛ የወጡትን በመለየት ለክልሉ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ በዕጩነት ካወዳደራቸው ኢንተርፕራይዞች መረጃ ጋር ይልካል፡፡

መ. እያንዳንዱ የክልል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየዞኑ ተመርጠው የተላኩለትን ኢንተርፕራይዞች በመስፈርቱ መሠረት በማወዳደር በጣም የተሻሉትንና ለክልሉ ሞዴል የሆኑ ከእያንዳንዱ ዋናዋና እና ከንዑስ የሥራ መስኩ አንደኛ የሆኑትን በመለየት በዕጩነት ካወዳደራቸው ኢንተርፕራይዞች ዝርዝር መረጃ ጋር ለፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፡፡

1) **የአዲስ አበባ ከተማን በተመለከተ፡-**

ሀ. የወረዳ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለክ/ከተማው የጥ/አ/ኢ/ል ጽ/ቤት

ለ. የክፍለ ከተማው የጥ/አ/ኢ/ል ጽ/ቤት ለከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢን/ል/ኤጀንሲ

ሐ. የከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየሥራ መስኩ አንደኛ የወጡትን ለፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፡፡

አዲስ አበባ

2)የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርን በተመለከተ፡-

ሀ. የቀበሌ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ጽ/ቤት ለከተማው ጥ/አ/ኢ/ል/ኤጀንሲ፤

ለ. የከተማው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየ/ሥራ መስኩ አንደኛ የወጡትን ለፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ይልካል፡፡

ሐ. የፌደራል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከየክልሉ ተመርጠው የተላኩለትን ኢንተርፕራይዞችን መረጃ አጣርቶ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውንና ዋና ዋና ክልሎችን በሁለት በመክፈል ከእያንዳንዱ ዋናዋና እና ንዑስ የሥራ ዘርፉ ከ1-3 የወጡትን ኢንተርፕራይዞቹ ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይልካል፤

2) የቴክኒክና የሙያ ተቋማት

ሀ. የክልሉቹ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት የየክልላቸውን የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ተቋማትን በማወዳደር ክልሉን የሚወክሉ ሶስት ሞዴል ተቋማት በመለየትና እና እንዲጸድቅ በማድረግ ለፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ያስተላልፋሉ፤

ለ. የፌዴራል ኤጀንሲው ከክልሎች ተለይተው የቀረቡለትን ሞዴል የቴክኒክና የሙያ ትምህርት ተቋማትን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት በሀገር አቀፍ ደረጃ በማወዳደር ምርጥ የሆኑትን ሶስት በመለየትና በማጸደቅ እውቅና እንዲሰጣቸው ለከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ይልካል፤

ሐ. አስተባባሪ ኮሚቴው በመከታተልና ሪፖርት በመቀበል የተለዩትን ሞዴል ተቋማት ስራቸውን የሚያሳይ አጭር ዶክመንተሪ ፊልም እንዲቀርብ በማድረግ ለቴክኒክ ኮሚቴው ያስተላልፋል፤

መ. በመጨረሻም በቴክኒክ ኮሚቴው አማካይነት ለዓብይ ኮሚቴ ቀርቦ እንዲጸድቅ ይደረጋል

## ክፍል አራት

## የመተባበርና የመቀናጀት ሁኔታ

### 28.አስተባባሪ አካላት

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተጠቀሱት አካላት የተሰጣቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለማድረግ የከተሞች ሳምንት አዘጋጅ ኮሚቴው ያስተባብራል፤ ያቀናጃል፤

### 29. የመወዳደሪያ ወቅት

እውቅናው በየዓመቱ የሚሰጥ በመሆኑ በእያንዳንዱ ዓመት ለውድድር የሚወሰደው መረጃ ያለፈውን በጀት ዓመት መረጃ ይሆናል፤

## 30. የእውቅና ዓይነትና የሚኖረው ፋይዳ

1) የእውቅናው ዓይነት በሰርቲፊኬትና ተቋማትን መሰረት አድርጎ በሚዘጋጀው ማቴሪያል ይሆናል፣

2) እውቅናው የሚኖሮው ፋይዳ ተሸላሚ ተቋም እንደ ሞዴል ተቋም ስለሚታይ ተሞክሮው ተቀምሮ ለሌሎች እንዲሰፋ ይደረጋል፣

## 31. መመሪያው የሚጸናበት ቀን

ይህ መመሪያ ጳጉሜ 5 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ ተ/ ማርያም

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

አባሪ-1

የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መመዝገቢያ ቅጽ፤

ክልል________ ዞን________ ከተማ________ ወረዳ/ቀበሌ________

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | የተሰማራበት የሥራ መስክ | የተቋቋመበት ዓመት | የሰው ኃይል ብዛት | | የካፒታል መጠን | | የሚያመርታቸው ዋና ዋና የምርት ዓይነቶች/አገልግሎቶች | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ሲጀመር | አሁን | ሲጀመር | አሁን | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

የመዝጋቢው ስም________ ያረጋገጠው ኃላፊ ስም________

ኃላፊነት________ ኃላፊነት________

ፊርማ________ ፊርማ________

አባሪ 2.

የሞዴል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ማወዳደሪያና መምረጫ ቅጽ፤

| ተ.ቁ | የኢንተርፕራይዙ ስም | በዘርፉ ሥራ የቆይታ ዘመን | በመነሻና በወቅቱ ካፒታል መካከል ያለው ልዩነት | ኢንተርፕራይዙ ያሰማራው ተጨማሪ የሰው ኃይል ብዛት | የተለየ ቴክኖሎጂ የመጠቀም ሁኔታ | ምርታማነት | የምርት ጥራት | በሞዴልነት ሲመረጡ ያገኙት ውጤት | ድምር | መግለጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 10% | 20% | 15% | 15% | 10% | 10% | 20% | 100% | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |

<u>የመልማይ ኮሚቴ አባላት ስም</u> — <u>ፊርማ</u>

1. ______________________ ____________
2. ______________________ ____________
3. ______________________ ____________
4. ______________________ ____________
5. ______________________